# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ህዳር 4ቀን 2003 ዓ.ም.**

**በአዲስ አበባ መስተዳደር ውስጥ ሹምሽር ተከሄደ**

**በኦጋዴን ውስጥ ያለው ውጥረት እንደገና አገረሸ**

**የመለስ አገዛዝ መሬት የመሸጡን ሴራ ቀጥሎበታል፤ሕዝቡም ተቃውሞ እያደረገ ነው**

የወያኔ ቡድን እድገት እና ትራንስፎርሜሽን በሚል ሰበብ የራሱን ካድሬዎች ከስልጣናቸው እያባረረና ለፍርድ እንዲቀርቡ እያደረገ መሆኑ ታወቀ።

ዓርብ ዕለት ህዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም የአዲስ አበባ መስተዳድር 3ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በሚል ባለስልጣናቱን ሰብስቦ ውይይት ያደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ድንገተኛ ሹም ሽር አድርጎዋል።

በዚህም መሰረት የአዲስ አበባ ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ፤ምክትል አፈ ጉባዔውን እንዲሁም ዋና ጸሀፊውን ከስልጣናቸው እንዲነሱ የተወሰነባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ አፈ ጉባዔ ዶክተር አፀደ አሰፋ የተባለችው በፈፀመችው ከባድ ወንጀል ያለ መከሰስ መብትዋ እንዲነሳ ተብሎ ተባርራለች።

አፈ ጉባዔዋን ከባድ ወንጀል በመፈጸምሽ ...... ምክትል አፈ ጉባዔውን እና ዋና ጸሃፊውን ደግሞ ከስራ ብቃት ማነስ በሚል ሰበብ ከስልጣናቸው እንዲባረሩ የተደረገ ሲሆን በተለይ አፀደ የተባለችው ግለሰብ ጉዳይዋ ወደ ፍርድ ቤት እንዲሄድ ተደርጎዋል።

በተነሱት ባለስልጣናት ምትክ ከአፈ ጉባዔዋ ቦታ በስተቀር በሌሎቹ ቦታ ሹመት የተሰጠ ሲሆን በተለይ የአፈ ጉባዔውን ቦታ የሚወስደው በብሔር ተዋጽኦ ስለሆነ ታስቦበት ሊሰጥ ይገባል በሚል በይደር የታለፈ መሆኑም ታውቆዋል።

ከነዚህም በተጨማሪ የአዲስ አበባ መስተዳድር የጤና ቢሮ ኃላፊ፤የመስተዳድሩ የፋንይናንስ እና ኢኮኖሚ ቢሮ ኃላፊ፤የትራንስፖርት እና መንገድ ቢሮ ኃላፊ የአቅም ግንባታ በሮ ኃላፊዎች አዲስ ሹመት የተሰጠ ሲሆን የቀድሞዎቹ ኃላፊዎች ገሚሱ ከስልጣኑ ሲባረር ሌሎቹ ደግሞ ወደ ክልል እና ፌዴራል ቢሮዎች ተዛውረዋል።

በወያኔው ሹም በኩማ ደመቅሳ የሚመራው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ሰሞኑን በጀመረው መሬት ነጠቃ ምክንያት ህጋዊና ህጋዊ ያልሆኑት ተለይተው እርምጃ ቢወሰድ የተሻለ ነው በሚል በተነሱ የውስጥ ክርክሮች የተነሳ በባለስልጣናቱ መሀከል ፍጭት ተጀምሮ እርስ በርስ ሰታመሱ የከረሙ ሲሆን በቅርቡም ዳግም ምንጠራው ሊከተል እንደሚችል ተጠቁሞዋል።

የወያኔ ቡድን ሰሞኑን የኦብነግን አከርካሪ መትቼ ጣልኩ የሻዕቢያን እና የአልሻባብ ተላላኪነቱን መንገድ በጥሼ ጥያለሁ እያለ የሀገሪቱን በቴሌቪዥንና አይን በራዲዮ ጆሮ ሲያደነቁር የነበረ ቢሆንም ሳምንት ባልሞላ ግዜ ውስጥ አጥፍቼዋለሁ ካለው ቡድን ጋር ውጊያ መግጠሙ ተጋለጠ።

ለሁለት ሳምንታት እጅግ አሰልቺ እና መንቻካ ፕሮፓጋንዳ ሲያደርግ የሰነበተው የወያኔ ቡድን የኦብነግ ተዋጊ ኃይሎች እጃቸውን ሰጥተው ወደ ሰላማዊ ኑሮ ተመለሱ በማለት ሲለፍፍ የሰነበተ ቢሆንም በዚሁ ባሳለፍነው ሳምንት ግን ከአንዱ አንጃ ከተባለው የኦብነግ ጦር ጋር ውጊያ ማድረጉን ድርጅቱ ባወጣው መግለጫ አስታውቆዋል።

እራሱን የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጭ ግንባር ነኝ ብሎ የሚጠራው ይሄው የወያኔ ተፋላሚ ቡድን ማክሰኞ እለት ባወጣው መግለጫ በኦጋዴን ውስጥ በወያኔ ጦር ላይ በወሰድኩት ድንገተኛ እርምጃ ከ267 ወታደሮች በላይ ገድዬ ብዙዎችን አቁስያለሁ በማለት የገለፀ ሲሆን ወያኔ በበኩሉ ውሸት ነው ሲል ምላሽ ሰጥቶዋል።

ወያኔ ሙሉ ለሙሉ ምስራቅ ኢትዮጵያን ከታጣቂ ተዋጊ ኃይሎች ነፃ አውጥቻለሁ ቢልም በአካባቢው ለነዳጅ ቁፋሮ የተሰማሩ ድርጅት ሰራተኞች ግን ከፍተኛ የተዋጊ እንቅስቃሴ እንዳለና በቅርቡ ከስፍራው ለቀን እንድንወጣ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ እየሰጡን ነው በማለት መግለፃቸውን እና የቁፋሮ መሳሪያቸውን እያስወጡ መሆኑን የዘገበን ሲሆን በቅርቡም በወያኔ ጦር ላይ ጥቃት ሰንዝሮ ድል ማስመዝገቡን ድርጅቱ ባወጣው መግለጫ አስታውቆዋል።

የሱማሌ ክልልን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ የራሱን መንግስት ለማቋዋቋዋም የሚንቀሳቀሰው ኦብነግ የተሰኘውና በቀድሞው የሶማሊያ መንግስት የባህር ኃይል አዛዥ አድሚራል ሞሐመድ ኦማር ኦስማን የሚመራው ቡድን ድንገተኛ ጥቃት አደስኩ ከማለቱም በተጨማሪ አሁንም በክልሉ በስፋት እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ባወጣው መግለጫ ላይ አትቶዋል።

ወያኔ በሻዕቢያ ሰልጥነው በሱማሌ ላንድ በኩል ሰርገው የገቡትን የኦብነግ ተዋጊዎች ማረኩኝ ብሎ ከራሱ ጋር ትስስር ያላቸውን የሱማሌ ተወላጆች በቲሌቪዥን አቅርቦ ለሁለት ሳምንታት ሲወተውት የከረመው ወያኔ ግለሰቦቹ በንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው ለወያኔ የሚሰልሉ መሆናቸውንም ከጅጅጋ የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል።

በጅጅጋ እና በሀርቲሼክ ከፍተኛ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ የሚካሄድ ሲሆን ይሄንኑ ተከትሎ ሰርጎ ገቦች ሊገቡና ጥቃት ሊያደርሱብኝ ይችላሉ በሚል ስጋት ተማረኩ የተባሉትን ሰዎች ከአራት ዓመት በፊት ጀምሮ ትናንሽ ሱቆችን ከፍቶላቸው የስለላ ስራ እንዲሰሩለት የመደባቸው መሆኑንና አሁን ደግሞ ማጣፊያው ሲያጥረው መልሶ እነሱኑ ማረኩኝ ብሎ በቲሌቪዥን ማቅረቡ አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ተብሎዋል።

ባሳለፍነው ወር መጀመሪያ ላይም ቢሆን ከአዋሽ አርባ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ ሸራ ለብሰው የነበሩ ከባድ የጦር መሳሪያዎች ወደ ስፍራው የተጉዋጉዋዘ መሆኑ ሲገለፅ የምስራቅ እዝ ዋና አዛዥ የሆነው ሜ/ጄ/ል አብርሀ ወ/ማርያም በበላይነት የሚመራው የምስራቁ ግንባር በሶስት ክፍለ ጦሮች ተከፍሎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑና አንደኛው ክፍለ ጦር ሱማሊያ ውስጥ ዘልቆ መግባቱን ሁለቱ ክፍለ ጦሮች ደግሞ በኦጋዴን ውስጥ ተበትነው ያሉ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል።

***የመለስ ዜናዊ ከሀዲ ቡድን ኢትዮጵያን ለመሸጥ የጀመረውን አሳፋሪ ሴራና ድርጊት ቀጥሎበታል። መለስ ዜናዊ 3 ሚሊዮን ሄክታር ለም መሬት ማለትም የአውሮጳ ሀገር የሆነችውን ቤልጅየምን የሚያክል መሬት ለባዕዳን ሊሰጥ ወስኗል። በዚህም መሰረት ለቻይናና ህንድ ኩባንያዎች፣ ለሳውዲ አረቢያና ተወካያቸው ለሆነው አላሙዲ፣ ይባስ ብሎ ደግሞ ለግብፅም ሳይቀር ብዙ ሺ ሄክታር መሬትን አሳልፎ ሰጥቷል። ግብፅ በአባይ የተነሳ የሀገር ጠላት ሆና ሳለ ባበሀር ዳር መሬተ ተለግሶታል። መለስ ዜናዊ በመሰረቱ ኢትዮጵያን የሚጠላ ግለሰብ መሆኑን በተደጋጋሚ ያጋለጠ ነውና በዚህ ድርጊቱ የሚገረም የለም። ዝም እስከተባለ መላ ሀገሪቷን--ከራሱ ከክልል አንድ በስተቀር--ለቅርጫ ማቅረቡ የሚጠበቅ መሆን አለበት፡ በሰሞኑ በሱሉልታ የታየው የሕዝብ ተቃውሞ አቅጣጫን ጠቋሚ ነው። የመለስ ቡድን ለም መሬትን ለባዕዳን ማስረከቡንና ይህም ክህደት መሆኑን ለመሸፈን ልዩ ልዩ ማደናገሪያዎን ያሰማል። ባዕዳኑም ይህን ሀሰት ያስተጋቡለታል። ለምሳሌ ከ 312 ሺ ሄክታር መሬት በላይ ለም መሬት በርሽ የተረከበችው ህንድ በጋንቤላ የተመራሁት መሬት ሰው የለበትም፣ ምድረ በዳ ነው ልትል ሞክራለች። መለስ ለሱዳን የሰጠውን መሬት በዚህ መልክ ማጠየቂያ ሊሰጥ ሞክሮ እንደነበርም የሚታወስ ነው። በሀገራችን ረሀበ ስፍኖ እያለ ለም መሬትን ከሕዝብ እያቀማ ለባዕዳን የሚሰጠው የመለስ ሸፀቡድን ከዚህ ሂደት ሕዘብና ሀገር የሚጠቀሙ አድርጎ ለማቅረብ ነጋ ጠባ እየሞከረ ነው።ሀቁ ግን ሌላ ነው። የሀገር ለም መሬት ለባዕዳን ከመሰጠቱ ሕዝብ እያተረፈ ያለው ቅንጣት ነገር የለም። የህንዱ ካርቱሪ ኩባንያ ለምሳሌ ብዙ መቶ ሺ ኩንታል ሩዝ፣ ወዘተ በኢትዮጵያ አምርቶ ምስራቅ አፍሪካን***

ሊያጥለቀልቅ መሰናዳቱን ሳይደብቅ ገልጿል። ለጅቡቲ ብቻ 40 ሺ ቶን ሩዝ ከኢትዮጵያ አምርቶ መሸጡን ተናግሯል። ማለትም ባዕዳን የሚያመር ቱትን ለኢትዮጵያ መንም አይጠቀማትም--ምርታቸውን ወደ ሀገራቸው ወይም ወደ ውጭ ገበያ ይወስዳሉና ነው። ባዕዳኑ ክሊነከ ትምህርት ቤት እንከፍታለን፣የሕዝብ ኑሮ ን ለማሻሻል እንጥራለን ያሉትም ተግባራዊ ያልሆነ ባዶ ቃል መሆኑም እየታየ ነው። የራሳቸውን ፖለቲካና ሀይማኖት በከረረ መልኩ የሚያሰራጩት እንደ ቱርክ ዓይነቶቹ ሀገሮችም ለሀገር የሚበጁ አይደሉም። ግብፅ በበኩሏ በአባይ የተነሳ የኢትዮጵያ መገነጣጠል ይበጀኛል እያለች ባለችበት በባህር ዳርና ሌሎች ቦታዎች መሬት መስጠት ምን ቢባል ምን ለሀገር ከቶም የሚጠቅም አይደለም። ሀገረን አሳልፎ መስጠት ነው ለጠላት። በመሆኑም ሕዝብ ይህን ሂደት በዝምታ ወይም በአርምሞና ቁጭት ማየት ሳይሆን ሆ ብሎ በስልትበመነሳት በባዕዳኑ ላይም እርምጃ በመውሰድ ይህን የሀገር ለም መሬት ዘረፋ ማቆም አለበት። ይህን ዓይነት ቆራጥ እርምጃ ከተወሰደ ባዕዳን በመጡበት ፈርጥጠው ይመለሳሉ። አለበለዚያ ግን ከወያኔ ሰምረው ሕዝብን እየናቁ ብዝበዛቸውን ይቀጥላሉ። ሡዜጎች በጋራም ሆነ በተናጠል ሀገራቸውንና መሬታቸውን ማስከበር አለባቸው እንጂ የመለስ ከሀዲ ቡድን መላ ኢትዮጵያን --ከትግራይ በመለስ-- ሊሸጥ ሊለውጥ ወስኗል። ለዚህም ነው ታግለን ልናከሽፈው የሚገባን።

ፀረ ኢትዮጵያው የመለስ ቡድን በደርግ ጊዜ ሕዝብ ተርቦ፣ በተለይም ሕዝቤ የሚለው የትግራይ ሕዝብ በረሀብ ተጠቅቶ ባለበትና ሺዎች እየረገፉ ባለበት በረሀብተኛው መነገዱና ብዙ ሺዎችንም ለሞት መዳረጉ ተደጋግሞ የተጋለጠ ሀቅ ነው። ደርግን ማጋለጥ በሚል ከአሜሪካ ጋረ በመመሳጠር ብዙ ሺ የተራቡ የትግራይ ተወላጆችን ከትግራይ ወደመተማ ጎንደር አጠገብ (ወዲ ከውሊ ወደሚባል ቦታ አጓጉዞ) በመንገድ ላይም ሆነ በየቦታው ከደረሱ በኋላ ለሞት መዳረጉ ምስጢር አይደለም። ይህን አድርጎ ግን ብዙ ሚሊዮን ዶላር ለአሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ኖርዌይና ሌሎችም ሀገሮች አግኝቷል። በእርዳታ መልክያገኘውንም ገንዘብ 95 በመቶውን ለመሳሪያ ግዢና ለድርጅቱ መጠናከሪያ ማዋሉን በቅድሚያ ኢሕአፓ ያጋለጠ ሲሆን በወቅቱም ወያኔን ጥለው የወጡ አባሎቹም አጋልጠው እንደነበር የሚታወስ ነው። በቅርቡም የወያኔ መሪዎች የነበሩ ግለሰቦች ይህንኑ የነ መለስና ስብሐት ወንጀል ያጋለጡ ሲሆን ባዕዳንም የረሀቡ እርዳታ በወያኔ ለመሳሪያ ግዢና ለድርጅት ማጠናከሪያ መዋሉን መናገራቸው በዚህ እኩይ ተግባር የተሳተፉትንንባዕዳን ማስቆጣቱም ታውቋል። በእርዳታ ድርጅት ሽፋን ብዙዎቹ (ማለትም ኦክስፋምና ሴቭ ዘ ችልደረን እንግሊዝ፣ ዩኒሴፍ፣ ወርልድ ቪዥን፣ ኖርዌጂያን ካውንስል ኦፍ ቸርችስ፣ አይ አር ሲ፣ ወዘተ) ደርግን ለመጣል በሚል ወያኔና ሻዕቢያን መርዳታቸው የሚታወቅ ነው። ይህ እርመጃቸው በመጋለጡ የበገኑት ክፍሎች ድርጊታቸውን የካዱ ሲሆን ወያኔም በበኩሉ ቅጥረኛቹን አሰልፎ ሊከላከል ተወራጭቷል። የሚያሳዝነው ደግሞ መለስንተቃዋሚ የሚሉ በመድረከና አረና ደረጃ ያሉ የቀድሞ ወያኔዎች ይህን በተመለከተ ሀቁን መናገር

*ማፈራቸው ነው:: የእንገሊዝ ራዲዮ ጣቢያ ቢቢሲ ወያኔ ገንዘቡን ለመሳሪያ ግዢ ተጠቅሞበታል ብሎ ያስተላላፈውን ሀቅ እንዲክድ/እንዲስብ በእንግሊዝ መንግሰትና በወያኔ ተባባሪ በነበሩ ግብረ ሰናዮች ጫና ስለተደረገበት ተሳስቻለሁ ብሎ ይቅርታ ጠይቋል:: የሌባ ዓይነ ደረቅ እንዲሉም የመለስ ቡድን አኔ ራሴ ይቅርታ ልጠየቅ እያለም ነው:: ወያኔ እንኳን ይቅርታ ሊጠየቅ ቀርቶ ለዝቡ ሺዎች የትግራይ ረሀብቶች ሞት ሊጠየቅ ሊከሰስ የሚገባው ጨካኝ ቡድን ነው:: ቢቢስ ተሳሳትኩ ያለው በአንግሊዝ መንግስት ተፅዕኖ ነው:: የእንግሊዝ መንግስት በአንድ በኩል ተገንጣዮችን በውስጥ ውስጥ እየደገፈ በይፋ ደግሞ የመለስን ሀገር አጥፊ ቡድንንም አቅፎ ያለ መሆኑም መታወቅ ያለበት ነው:: ለመለስ ዜናዊ የዓለም አቀፍ መድረክ ዳነኪራ በቅመያ ተጠያቂ አንግሊዝ መሆኗ የኒዘነጋ ወይም የሚካደ. አይደለም:: ለዚህም ነው የቢቢሲ ተሳስተናል ይቅርታ ልፈፋ ሀሰትና እልፎም አሳፋሪ የሚሆነው:: የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በቅርቡ በጉዳዩ ላይ ባወጣው መግለጫ ቢቢሲ ራዲየ ሀቁን ሰላወሳ ይቅርታ መጠየቅ መገደዱ አሳዛኝ ነው ሲል ተችቷል:: ሀቁ ግን ወያኔ በረሀበተኛው ስም ያገኘውን ገንዘብ ለራሱ ወሰዶና ተጠቅሞ ብዙ ሺ የትግራይ ረሀብተኞችን ለሞት መዳረጉ ነው::*

የሥር ፍርድ ቤት ያስተላለፈባቸውን የዕድሜ ልክ እሥራት ላይ ‹‹ቅር ተሰኝቻለሁ›› በሚል የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ በሞት እንዲቀጡለት ይግባኝ የጠየቀባቸው አምስት የግንቦት 7 ፍርደኞች አቤቱታ ውድቅ ተደረገ፡፡ በነፃ ተሰናብተው የነበሩትን አራት ተከሳሾች ደግሞ ጥፋተኛ እንዲባሉለት በጠየቀው መሠረት ጥፋተኛ ተብለዋል፡፡ የሞት ቅጣት ተጠይቆባቸው የነበሩት ብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ፣ አቶ አሳምነው ጽጌ፣ ሌተና ኮሎኔል ደምሰው አንተነህ፣ ሻለቃ መኮንን ወርቁና ሌተና ኮሎኔል አለበል አማረ (በሌሉበት) ናቸው፡፡ ይፌደራል ፖሊስ/ ኣዛዥ ይንብርው ኮለነል በኣሁኑ ጊዜ በአስመራ ይገኛል። ሌላው ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ፣ የአቶ አሳምነው ጽጌና የአቶ ጽጌ ሀብተማርያምን ንብረት እንዲወረስለት ሲሆን፤ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተብየው በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ፤ የአቶ ጽጌ ሀብተማርያም ንብረትን በሚመለከት ባደረገው ምርመራ ፍርደኛው በሥር ፍርድ ቤት ከተላለፈባቸው ውሳኔና ዕድሜያቸው ጭምር በቂ በመሆኑ ንብረታቸው ሊወረስ እንደማይገባ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

ብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ፣ የወያኔ አገዛዝ የሰጣቸውን ሥልጣን ወደ ጐን በመተው መንግሥትንና ሕገ መንግሥቱን በኃይልና በአመጽ ለመጣል ተሰልፈው ተገኙ በመባላቸው፣ እንዲሁም አቶ አሳምነው ጽጌ የወንጀሉ ጠንሳሽና አደራጅ መሆናቸው ተረጋጋጠ በመባሉና ሕጉም በከባድ ወንጀል ላይ የተሳተፈ በማስረጃ የተረጋገጠበት ሰው ንብረት እንደሚወረስ ስለሚያዝ፣ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ

ንብረታቸው የሌላ ወገንን ድርሻ በማይነካ ሁኔታ እንዲወረስ አዟል፡፡ ዓቃቤ ሕግ የሥር ፍርድ ቤት በነፃ ያሰናበታቸውን ሻለቃ ፋናዬ ውቤ፣ መቶ መለቃ አባቡ ተፈሪ፣ ኢንስፔክተር አራጋው አስፋውና አቶ ጌቱ ወልዴ ጥፋተኛ እንዲባሉለት ባመለከተው መሠረት ጥፋተኛ ተብለዋል፡፡ ዓቃቤ ሕግ የቅጣት አስተያየትም ሰጥቶ በነገው ዕለት ለቅጣት ውሳኔ ተቀጥረዋል፡፡